# ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

1ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ISBN ቁጥር -

ዋጋ ብር -

ሥነ-ጥበባት
የተማሪ መጽሐፍ
1ኛ ክፍል

# ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

1ኛ ክፍል



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# የጥንቃቄ መልዕክት

## ተማሪዎች!

## ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

ማሳሰቢያ፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

# ሥነ-ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ቀለመወርቅ ተገኜ አስማማው

ትግሌ ደስታ ምህረቴ

አርታኢ

አብዱ ሀሰን ፈንታው

ታደግ ማሞ ቸርነት

ቡድን መሪ

አሰፋ ሰማው ፈንታዬ

ሰዓሊና የሽፋን ገፅ ዲዛይን

ቀለመወርቅ ተገኜ አስማማው

የመዝሙር ግጥምና ዜማ ደራሲ

ትግሌ ደስታ ምህረቴ

ዲዛይነር

አትርሳው ጥግይሁን ወረቀት



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# ማውጫ


መግቢያ ........ ii

ምዕራፍ 1፡ አካባቢን ማስተዋል

1.1 አካባቢያችን ........ 2
1.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች ድምፅ ........ 2
1.3. በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ ........ 6
1.3.1 የቤተሰብ አባላት እንቅስቃሴ........ 7
1.3.2 የቤት እንስሳትና የአእዋፋት እንቅስቃሴ ........ 7
1.4 በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን በቪዲዮ መመልከትና ድርጊቱን መናገር ........ 11
1.5 በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ምስልና መልእክት መለየት........ 12

ምዕራፍ 2፡ የፈጠራ ችሎታን ማዳበር

2.1 የቤተሰብ ኃላፊነትን መግለፅ እና ማስመሰል ........ 17
2.2 ስለ ቤተሰብ መዘመር........ 19
2.3 መሞነጫጨር፣ መስመር መስራት፣ መሳልና መቀባት ........ 21
2.4 ከቀላል ምት ጋር ውዝዋዜዎችን በማቀናጀት መጫዎት........ 32

ምዕራፍ 3፡ ባህል

3.1 በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥበባት ........ 37
3.1.1 ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች........ 39
3.1.2 ባህላዊ ጨዋታዎች ........ 41
3.1.3 ተረት እና አፈ-ታሪክ........ 42
3.1.4 እንቆቅልሽ ........ 52
3.2 በዙሪያችን ያሉ ቀለማት ........ 52
3.2.1 የአልባሳት ቀለማት........ 52
3.2.2 አካባቢያዊ ቀለማት ........ 53

ምዕራፍ 4፡ ባህላዊ ተግባራትን ማድነቅ

4.1. ባህላዊ አለባበስ ........ 60
4.2 ባህላዊ ቁሳቁሶችን በመጠቀም መጫወት ........ 61
4.3 ባህላዊ ጭፈራን መጨፈር........ 63
4.4 ባህላዊ ተግባራትን መሳል ........ 64

ምዕራፍ 5፡ የሙዚቃ፣ የስዕልና የድራማ ግንኙነት(ዝምድና)

5.1 በቡድን መዘመር ........ 67
5.1.1 ስለ ቀለማት መዝሙር ........ 68
5.1.2 ስለ ስዕል መዘመር ........ 70
5.2 በቡድን መተወን........ 71
5.3 መዝሙርን ትወናንና ስዕልን ማገናኘትና መተግበር ........ 72

## መግቢያ

### ሥርዓተ ትምህርቱን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተካሂደዋል። ከእነዚህም አንዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተካሄደው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ዋናው ነው። ይህ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ርእሶች ዙሪያ የተካሄዱት ጥናትና ምርምሮች ሥርዓተ ትምህርቱ በይዘት የታጨቀ፣ በትምህርት አይነቶች ብዛት የተወጠረ፣ በአብዛኛው ይዘት ማስታዎስን ትኩረት ያደረገ፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ህይወትና ኑሮ፣ ምርታማነት እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀት ጋር ያልተቆራኘ፣ ተማሪዎች ተገቢውን ግብረገባዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበሱ ያላደረገ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እና ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ከማስተናግድ አኳያ ክፍተት ያለበት መሆኑ ተመላክቷል። በተጨማሪም ስርዓተ ትምህርቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማለትም ለመማር መማርን፣ በጥልቀት ማሰብና ችግር ፈችነትን፣ የፈጠራ አስተሳሰብና አዳዲስ ግኝቶች ማፍለቅን፣ ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ መሪነትና ውሳኔ ሰጭነትን፣ የቴክኖሎጂ እውቀትን እና የባህል ማንነትና አለማቀፋዊ ዜግነትን ማስጨበጥ የማይችል መሆኑን በማመላከት የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻል እና ለውጥ እንዲካሄድ የሚያመላክቱ ምክረ-ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግም ሰፊ የውይይት እና የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ህብረተሰቡ እንዲወያይ በማድረግ የለውጥ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ወደ ትግበራ ተገብቷል። ከእነዚህ የለውጥ መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ዝግጅት ተድርጓል።

በዚህም መሠረት አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚያግዙ ሰነዶች ማለትም የተማሪው የባህሪ ገጽታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፣ የይዘት ፍሰት፣ ተፈላጊ የመማር ብቃት እና መርሃ-ትምህርቶች እንደ ሀገር ተዘጋጅተዋል። በእነዚህ ሰነዶች መነሻነትም በክልላችን የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ-6ኛ) እና የመካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍሎች የየትምህርት አይነቶች የተማሪዎች መማሪያ እና የመምህራን ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል።

## የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል። ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል። በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል።

## ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል። መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል።

## ውድ ወላጆች/ አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል። በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ።

# ምዕራፍ 1

# አካባቢን ማስተዋል

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በቤትና በአካባቢያችሁ የምትሰሟቸውን ነገሮች ድምጽ ትለያላችሁ።
- በቤታችሁና በአካባቢያችሁ ውስጥ የምታዩዋቸውን ነገሮች የቀለም አይነት ትገልጻላችሁ።
- በቤታችሁና በአካባቢያችሁ ያሉ ነገሮችን ቅርፅ ትለያላችሁ።
- ምስሎችን በማስተዋልና በመመልከት ስላስተዋላችሁት ነገር ትናገራላችሁ።
- የተለያዩ ዉዝዋዜዎችን በመመልከት ታደንቃላችሁ።
- ካዳመጣችሁት መዝሙር በመነሳት መዝሙሩን በዜማ ታዜማላችሁ።
- የተመለከታችኋቸውንና የሰማችኋቸውን ነገሮች እንቅስቃሴያቸውንና ድምጻቸውን በማስመሰል ትሰራላችሁ።
- የቤተሰብ አባላትን፣ የእንስሳትንና የዕጽዋትን ልዩ ልዩ ተግባራት አስመስላችሁ ትተገብራላችሁ።

## 1.1 አካባቢያችን

**መዝሙር አንድ:-**
**አካባቢያችን**



መኖሪያችን ነዉ አካባቢያችን
መዝናኛችን ነው መደሰቻችን
ተሰባስበን ከጎረቤት ጋር፣
ከእንስሳት ከአእዋፋት ጭምር፤
እንኖራለን ተደጋግፈን።

## 1.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች ድምፅ

1. ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ የምን የምን ድምጽ ሰማችሁ?
2. በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ የምን የምን ድምፆችን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

### የቤት እንስሳት ድምፅ

**መዝሙር ሁለት**
**ትንሽ በግ አለኝ**



እኔ ትንሽ በግ
አለኝ፣
በግ አለኝ በግ አለኝ፣
እኔ ትንሽ በግ
አለኝ፣
አባቴ የሰጠኝ።

ድምጹ ሆዴን አባባ፣

አባባ አባባ፣

ድምጹ ሆዴን አባባ፣

ሲጮህ ሲል ባአአአ ባአአአአ።

## መዝሙር ሶስት

### ትንሽ ድመት አለችኝ



ትንሽ ድመት አለችኝ፣

አለችኝ አለችኝ፣

ትንሽ ድመት አለችኝ፣

እናቴ የሰጠችኝ።

ድምጿን እወደዋለሁ፣

ወደዋለሁ ወደዋለሁ፣

ድምጿን እወደዋለሁ፣

ስትለኝ ሚያዉ ሚያዉ።

## መዝሙር አራት

### ትንሽዬ ዉሻ አለኝ



ትንሽዬ ዉሻ አለኝ፣
ዉሻ አለኝ ዉሻ አለኝ፣
ትንሽዬ ዉሻ አለኝ፣
አባቴ የሰጠኝ።
ሲያየኝ ደስ ይለዋል፣
ደስ ይለዋል ደስ ይለዋል፣
እኔም ደስ ይለኛል፣
ድምጹን ያሰማኛል፣
ዉዉ ዉዉ ይለኛል።

## የአእዋፋት ድምፅ

## መዝሙር አምስት

### ወፏን እወዳታለሁ



ወፍዬ ደስ ትላለች፣
ትላለች ትላለች፣
ቀለሟ ያምረኛል፣
ድምጿ ይማርከኛል፣
በጠዋት ስትጮህ፣
ፂዉ ፂዉ እያለች፣
ታስደስተኛለች
ነፍሴን ታረካታለች።

## መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ምስሎች ከተመለከታችሁ በኋላ የሚያወጡትን ድምፅ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ

1. 

2. 

3. 

4. 

5.



## 1.3. በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ነገሮች መካከል ምን ምን ነገሮች ሲንቀሳቀሱ ተመለከታችሁ?
2. የተመለከታችኋቸው ነገሮች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ?

### መዝሙር ስድስት፡- እንቅስቃሴ

**እኔ ሁለት እግር አለኝ፣**

የሚያስኬድ የሚያንቀሳቅሰኝ፣

ዶሮም እንደኔው ናት ሁለት እግር አላት፣

በሁለት እግሮቿ ትንቀሳቀሳለች፣

ደግሞም ትሮጣለች። (4)

ቡችየ አራት እግር አላት፣

ስትሄድ ስትሮጥ ፈጣን ናት፣

ውርየም እንደሷ አራት እግር አላት፣

እሷም እንደ ቡቺ ስትሮጥ ፈጣን ናት፣
ወፍዋ እሷ ትለያለች
ከላይ ትበራለች።
ክንፎቿን ዘርግታ ትንቀሳቀሳለች። (2)

## 1.3.1 የቤተሰብ አባላት እንቅስቃሴ



## 1.3.2 የቤት እንስሳትና የአእዋፋት እንቅስቃሴ

### የቤት እንስሳት እንቅስቃሴ









# የአእዋፋት እንቅስቃሴ





## መልመጃ ሁለት

1. የሚከተሉት እንስሳት እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ








## 1.4 በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን በቪዲዮ መመልከትና ድርጊቱን መናገር







## 1.5 በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ምስልና መልእክት መለየት











## መልመጃ ሶስት

1. ከዚህ በላይ ከተቀመጡት ምስሎች ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. እናንተስ በአካባቢያችሁ ምን ምን ነገሮችን ታከናውናላችሁ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

✍ አካባቢያችን ማለት በምንኖርበት ዙሪያ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ ነገሮችን የያዘ ነው። በአካባቢያችን ከሚገኙ ነገሮች መካከል ቤቶች፣ እንስሳት፣ ሰዎች፣ አእዋፍ፣ እፅዋት፣ መኪናዎች፣ ጋሪዎች እና የመሳሰሉት ናቸው።

✍ ከነዚህም ነገሮች መካከል የራሳቸው የሆነ ድምጽ ያላቸው እንስሳት፣ ሰው፣ አእዋፉትና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ ነገሮች ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የምን የምን ምስሎችን አይታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ያያችኋቸውን እንስሳት እንቅስቃሴያቸውን በማስመሰል ተንቀሳቀሱ?
3. የሰማችሁትን የእንሰሳት ድምጽ አስመስላችሁ አሰሙ?
4. የቤተሰቦቻችሁን ድምጽ አስመስላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አሰሙ?
5. የምትወዱትን መዝሙር በጋራ በመዘመር ለመምህራችሁ አሰሙ?

# ምዕራፍ 2

# የፈጠራ ችሎታን ማዳበር

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የቤተሰብ አባላትን ኃላፊነት ትገልጻላችሁ።
- በጨዋታና በተለያዩ ተግባራዊ ሥራዎች ትሳተፋላችሁ።
- የቤተሰብ ኃላፊነትን ሚና በመዉሰድ እንደ አባት፣ እናት፣ እህት እና ወንድም ሆናችሁ አስመስላችሁ ትሰራላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮችን ድምጽ ዉዝዋዜና ምስል ታስመስላላችሁ።
- የእንስሳትንና ሌሎችን ልዩ ልዩ ተግባራት አስመስላችሁ ትሰራላችሁ።
- በመሞነጫጨር፣ ስዕሎችን በመሳልና በመቀባት ስሜታችሁን ትገልጻላችሁ።
- አካባቢያዊ ነገሮችን ምስላቸውን፣ ድምጻቸውንና፣ እንቅስቃሴያቸውን አስመስላችሁ ትሰራላችሁ።

## 2.1 የቤተሰብ ኃላፊነትን መግለፅ እና ማስመሰል









### መልመጃ አራት

1. የቤተሰብ ኃላፊነቶች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ።
2. ከዘረዘራችኋቸው የቤተሰብ አባላት ኃላፊነቶች መካከል እንደ ቤተሰብ አባላት በመሆን አስመስላችሁ ተጫወቱ።

## 2.2 ስለ ቤተሰብ መዘመር

**መዝሙር ሰባት**

**እናቴ**

ዉድዬ እናቴ የኔ አለኝታ፣
የማትሰለቸኝ በጧት በማታ፣
ዉድዬ የኔ እያለችኝ፣
ከራሷ በላይ ስታስብልኝ፣
ትወደኛለች እወዳታለሁ፣
ለዘለዓለም አከብራታለሁ።



## መዝሙር ስምንት

### አባቴ

አባቴ ለኔ መመኪያዬ፣
መከታዬ ነዉ ከለላዬ፣
ጥሮ ግሮ ያኖረኛል፣
ያስብልኛል ለኔ ይጨነቃል፣
ይወደኛል እወደዋለሁ፣
ለዘለዓለም አከብረዋለሁ።



## መዝሙር ዘጠኝ

### እህቴ

እህቴ ዉዴ አጫዋቼ፣
ከሷ ጋር ስዉል
ተዝናንቼ፣
አብረን ስንሆን
ስንጫዎት፣
ስንፈነድቅ ስንደሰት፣
ትወደኛለች እወዳታለሁ፣
ለዘለዓለም
አከብራታለሁ።



## መዝሙር አስር

### ወንድሜ

ወንድሜ ዉዴ የኔ አሳቢ፣
ለእኔ ልዩ ነዉ ተንከባካቢ፣
ይመክረኛል እሰማዋለሁ፣
በኔ እንዲደሰት አደርገዋለሁ፣
ይወደኛል እወደዋለሁ፣
ለዘለዓለም አከብረዋለሁ።



### መልመጃ ሰባት

1. ስለቤተሰቦቻችሁ የምታውቁትን መዝሙር ዘምሩ።
2. ከመዝሙሩ ምን ምን መልእክት እንደተረዳችሁ አብራሩ።

## 2.3 መሞነጫጨር፣ መስመር መስራት፣ መሳልና መቀባት







## መስመር መስራት













### መልመጃ አምስት

1. በተለያየ አቅጣጫ እርሳሳችሁን በማንቀሳቀስ የተለያዩ መስመሮችን ደጋግማችሁ ስሩ።

## ዝርግ ቅርፅ መስራት











## ዝርግ-ቅርጾችን ቀለም መቀባት











## መልመጃ ስድስት

1. የተለያዩ ዝርግ ቅርፆችን በፈለጋችሁት የቀለም አይነት በጥንቃቄ ስሩ።
2. የሰራችኋቸውን ዝርግ ቅርፆች በጥንቃቄ ቀለም ቀቧቸው።

## 2.4 ከቀላል ምት ጋር ውዝዋዜዎችን በማቀናጀት መጫወት

### መዝሙር አስራ አንድ

### እንሽከረከራለን

እጅ ለእጅ ተያይዘን፣
እንሽከረከራለን፣
መዘመር እንችላለን፣
መደነስ እንችላለን፣
እጅ ለእጅ ተያይዘን፣
እንሽከረከራለን።



### መዝሙር አስራ ሁለት

### እናጨበጭባለን

እጅ ለእጅ ተያይዘን፣
ወደ ፊት እንሄዳለን፣
ተላቀን እንቆማለን፣
እናጨበጭባለን፣
እጅ ለእጅ ተያይዘን፣
ወደ ኋላ እንሄዳለን፣
ተላቀን እንቆማለን፣
እናጨበጭባለን።

## መዝሙር አስራ ሦስት

## መዘመር መዘመር

መዝሙር መዘመር ያስደስታል፣
በባህሉ መጨፈር ያስደስታል፣
ከመሰንቆ ጋራ፣
ከከበሮ ጋራ፣
መዘመር በጣም ስሜት ይሰጣል፣
መዘመር መዘመር ያስደስታል፣
ዳንስ መደነስ ያስደስታል፣
ከዋሽንትም ጋራ፣
ከክራርም ጋራ፣
መዘመር መዘመር ያስደስታል።

## መዝሙር አስራ አራት

## ወፎች ዘመሩ

ነፋስ መንፈስ ጀመረ፣
ዛፎች ተወዛወዙ፣
ቅጠሎች ረገፉ፣
ወፎችም ዘመሩ፣
ተራ ላ ላ ላ ላ ላ ላ፣
ተራ ላ ላ ላ ላ ላ ላ፣
የወፎችን ዜማ መስማት፣
ያስደስታል በጠዋት።



## መዝሙር አስራ አምስት፡-ሽርሽር እንሂድ

ጠዋት ተነስተን ሁላችን፣
ሽርሽር እንሂድ በእግራችን፣
ወንዝ ተሻግረን አልፈን፣
ጫካና ሜዳውን አቋርጠን፣
በአበቦች መሀል አልፈን፣
በነፋሻ አየር ተዝናንተን፣
ሳይመሽ ወደ ቤት እንመለሳለን።

### የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ✍ ይህ ምዕራፍ የፈጠራ ችሎታን በመዝሙር፣ በትወና እና በስዕል ስራዎች መግለጽ እንደሚቻል ያየንበት ነው። የቤተሰብ ኃላፊነትና ተግባራትን በማወቅና በማስመሰል በትወናና በመዝሙር የተገበርንበት ነው። ከቤተሰቦቻችን ኃላፊነት በተጨማሪ ስለምንወዳቸው ቤተሰቦቻችን በመዝሙር ፍቅራችንን የገለፅንበት ነው። ስለዚህ ቤተሰብንና የቅርብ ጓደኛን ወይም ዘመድን በመዝሙር ማመስገንና ፍቅራችንን መግለጽ እንችላለን።
- ✍ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው እርሳሶችን በመያዝ ከወረቀታችን ላይ በመሞነጫጨር የተለያዩ መስመሮችን በመስራት መለማመድ የእጅ ጽህፈታችንን የስእል ችሎታችንን ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህንንም ለማዳበር የተለያዩ መስመሮችን በማገጣጠም ከሰራን በኋላ የተለያዩ ቀለማት በመቀባት መስራት ይቻላል። ይህንን ማድረጋችን ስለ ቀለማትና ልዩ ልዩ አካባቢያዊ ነገሮች ያሏቸውን ቅርጽና ቀለም ለማወቅ ይጠቅማል።

✍በቀላል ሙዚቃዊ ምቶች በመጠበቅ ከጓደኞቻችን ጋር መጫወት የሙዚቃና የመዝሙር ችሎታችንን ያዳብራል። በዚህም ምክንያት በቀላሉ የአካባቢያችንን ባህላዊ ሙዚቃዎች እንድንጫወት ያግዘናል።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቤተሰብ አባል ኃላፊነትን በመናገር ኃላፊነቱን በማስመሰል ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አሳዩ።
2. እርሳስን በመጠቀም የፈለጋችሁትን መስመር በመስራትና ዝርግ ቅርጽ በመስራት ቀለም ቀብታችሁ አሳዩ።
3. የሚያስደስታችሁን መዝሙር በመዘመር ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ።

# ምዕራፍ 3

# ባህል

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የአካባቢያችሁን ባህል የሚገልፁ የባህል አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ።
- በአካባቢያችሁ ውስጥ የሚዘወተሩ ባህላዊ ጭፈራዎችንና ዘፈኖችን በመለየት በተግባር ትሰራላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚሰሩ የባህላዊ ጥበባት ውጤቶችን ትዘረዝራላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊ ቁሳቁሶችን ቀለማት ትለያላችሁ።
- በአካባቢያችሁ ውስጥ የሚገኙ ጥበባትን ታደንቃላችሁ።

## 3.1 በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥበባት

### የብረታ ብረት ስራ



### የሸክላ ስራ



### የስፌት ስራ





## ባህላዊ አልባሳት







## መልመጃ ስምንት

1. ባህላዊ ዘፈኖችን በቡድን በመሆን ዝፈኑ።
2. ባህላዊ ጭፈራዎችንና ጨዋታዎችን በቡድን በመሆን በባህሉ መሰረት ተጫወቱ።

### 3.1.1 ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች





**ባህላዊ የልጆች ዘፈን**

**አበባየሁሽ**

ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን ------እማማ አሉ ብለን ፣

ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን ---------አባባ አሉ ብለን፣

አበባየሁሽ ለምለም (2)-------

ባልንጀሮቼ --ለምለም ----------ቁሙ በተራ --ለምለም፣

እንጨት ሰብሬ --ለምለም --------ቤት እስክሰራ --ለምለም፣

እንኳን ቤትና- -ለምለም-------የለኝም አጥር --ለምለም፣

እደጅ አድራለሁ --ለምለም------ኮከብ ስቆጥር --ለምለም ፣

ኮከብ ቆጥሬ --ለምለም------------ስገባ ቤቴ --ለምለም፣

ትቆጣኛለች --ለምለም------------ውዷቷ እናቴ --ለምለም።

የመስቀል ለታ --ለምለም---------የዳመራዉ --ለምለም፣

ንፍሮ ቀቅዬ --ለምለም-----------ብላ ብለዉ --ለምለም፣

ጉልቻ አንስቶ --ለምለም --------ጎኔን አለዉ --ለምለም፣

ከጎኔ ጎኔ --ለምለም --------------ኩላሊቴን --ለምለም፣

እናቴን ጥሯት --ለምለም ----------መድሃኒቴን --ለምለም፣

እሷን ካጣችሁ --ለምለም-----------መቀነቷን --ለምለም፣

ማእዛዉ ይሸታል --ለምለም-----------እሷን እሷን --ለምለም።

አደይ የብር ሙዳይ ኮለል በይ(2)

ሸቴ አበባሽ ሸቴ አበባዬ አዬ ሸቴ አበባዬ

ሸቴ አበባሽ ስትለኝ ከርማ አዬ ሸቴ አበባዬ

ጥላኝ ሄደች በሀምሌ ጨለማ አዬ ሸቴ አበባዬ።

## 3.1.2 ባህላዊ ጨዋታዎች







### 3.1.3 ተረት እና አፈ-ታሪክ

## ተረት አንድ፡- የነሰላም ፎቶ



ሰላምና ተስፉ የተባሉ እህትና ወንድም ነበሩ። አባታቸውን ፎቶ እንዲያነሳቸው ጠይቀው ለመነሳት ወደ አረንጓዴ ቦታ ወስዶ እንዲዘጋጁ አደረገ።



በፎቶ ማንሳት ሙያ መሰረት በትክክል እንዲቀመጡ ካደረገ በኋላ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተንቀሳቀሰ አቅጣጫውን ሲያስተካክል ቆየ።



ነገር ግን በተለያየ አቅጣጫ ሲንቀሳቀስ የአበባ አጥር አደናቅፎት ወደ ኋላ ሲወድቅ እነሰላም ተደናግጠው ወደ አባታቸው ሲሄዱ ከአበባ ላይ ስለወደቀ አለመጎዳቱን አረጋገጡ። የወደቀበት ቦታም በጣም የሚያማምሩ አበቦች ላይ ነው።



የፎቶ ካሜራው ከሳር ላይ ስለወደቀ አልተሰበረም። ሰላም ፎቶ ማንሳትን ከአባቷ ስለተማረች አባቷ በአበቦች ላይ ተኝቶ ስታየው ከአበቦቹ ጋ ፎቶ አነሳችው።



ሰላም አባቷን ያነሳችው ፎቶ ወደ ፎቶ ማተሚያ ቤት ተወስዶ ታትሞ ሲታይ በጣም የሚያምር ፎቶ ሆነ።

# ተረት ሁለት፡- ታዛዧ ዉሻ



ሰለሞንና ነፃነት አንዲት ዉሻ ነበረቻቸው። ለዉሻይቱ የሚሆን ቤት ሰለሞን ሲሰራ ዉሻይቱም ታዛዥ ስለነበረች ለመስሪያ የሚሆነውን ጣውላ ታቀብለው ነበር።



ሰርቶ እንደጨረሰም ዉሻይቱ ከቤቷ ገባች። ዉሻዋ ቤቷ እንዲያምርላትና ደስተኛ እንድትሆን አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ቤቱን ሲቀባላት ከቤቷ ብቅ ብላ በማየት ሰለሞንን በጣም አመሰገነችው።



ዉሻው እንዳትቆሽሽና እንዳትታመም ሰለሞን የዉሻውን ንጽህና ሁልጊዜ ይጠብቃል። ሰኞ እለት በጠዋት ትምህርት ቤት ከመሄዱ በፊት የዉሻውን ገላ በሳሙና አጠበ።



ሰለሞን ወደ ትምህርት ቤት ሊሄድ ሲልም ዉሻይቱ ሰለሞንን ትወደው ስለነበረ አብሬ እሄዳለሁ ብላ ስትከተለው እንድትመለስ ሲጠይቃት ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆን አለች። በዚህም ምክንያት አኮረፈች።



ይህንን ያየችው ነፃነት ዉሻይቱ እንድትመለስ በመንገርና ማኩረፍ እንደሌለባት በመምከር ስታስረዳት እሺ ብላ ተስማማች።



ነፃነትም የአመቱ የመጀመሪያው ወር መስከረም ስለነበር አደይ አበባ ለመቁረጥ አካባቢያቸው ከሚገኝ ለምለም ቦታ ስትሄድ ከዉሻይቱ ጋር አብረው ሄዱ። አካባቢያቸውን ከቃኙ በኋላ አደይ አበባ ቆርጠው ወደ ቤት ተመለሱ።



ሰለሞንም ከትምህርት ቤት እንደተመለሰ ነጻነት የተገዛላትን የፊደል ገበታ እያጠናች ስለነበረ ሰለሞን ዉሻዋን መገቧት። ዉሻይቱም ባጠፋችው ጥፋት ተጸጽታ ይቅርታ ጠየቀች። ምግብ ስለሚመግባትና ስለሚንከባከባት አመሰገነችው። ከዚህ በኋላ ምንም ጥፋት እንደማታጠፋ ቃል ገባችለት።

# ተረት ሶስት፡- የተዋበ መንደር



አለሙና ሂዋን መምህራቸው አካባቢያቸውን ማፅዳትና ችግኞችን፣ ፍራፍሬዎችን እና አበቦችን መትከል ያለውን ጠቀሜታ ስላስተማረቻቸው አካባቢያቸውን ለማፅዳትና ለመንከባከብ ወሰኑ። በመሆኑም ሁለቱም በእረፍት ቀናቸው ቅዳሜና እሁድ አካባቢያቸውን ለችግኝ መትከያ ምቹ እንዲሆን አፀዱ።



እንዲሁም አካባቢው ለመኖር ተስማሚ እንዲሆን በማለትና በተማሩት መሰረት ለመትከል የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በመሄድ የተለያዩ ችግኞችን፣ ፍራፍሬዎችንና አበቦችን በጋራና በትብብር ተከሉ።



የተከሏቸው እንዳይደርቁ ውሃ በማጠጣት እና በመንከባከብ አበቦችና ዛፎች እንዲያድጉ አደረጉ። በዚህም የተነሳ አካባቢያቸው ውብ ሆነ።



አለሙና ሂዋን የተከሏቸውን አበቦችና ዛፎች እየተዘዋወሩ ተመለከቱ። ችግኞቹ፣ ፍራፍሬዎቹና አበባዎቹ አድገውና ለምልመው ሲመለከቱ በጣም ተደሰቱ።



አለሙና ሂዋን የተከሏቸው ፍራፍሬዎች በማፍራታቸው በመልቀም ለምግብነት ሲጠቀሙ አበቦችን ደግሞ ለተለያዩ በዓላትና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ቤታቸውን ለማስዋብ ይጠቅማሉ። የአለሙና የሂዋን አካባቢ በአረንጓዴ ተክሎች የተዋበና አስደሳች ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከአትክልቶቻቸው ጋር በደስታና በውበት መኖር ጀመሩ።

### መልመጃ ዘጠኝ

1. የምታውቁትን ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አውሯቸው።
2. ካወራችሁት ተረት ምን እንደተማራችሁ አብራሩላቸው።

## 3.1.4 እንቆቅልሽ



እንቆቅልሽ ------------ምን
አዉቅልሽ
ከአባቴ ጓሮ ፍልጥ ተደርድሮ
እንቆቅልሽ ------------ምን
አውቅልሽ
ላዩ በድን ታቹ በድን መሃሉ ነፍስ
አድን

## 3.2 በዙሪያችን ያሉ ቀለማት

### ጨዋታ፡-አረንጓዴ አረንጓዴ

አረንጓዴ አረንጓዴ አረንጓዴ................በክብ መሮጥ

ቢጫ............መቆም

ቀይ.............መቀመጥ

በትክክል ያልሰራ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። እስከ መጨረሻ ያልተሳሳተ አሸናፊ ይሆናል።

## 3.2.1 የአልባሳት ቀለማት

|  |  |
|---|---|





## 3.2.2 አካባቢያዊ ቀለማት

### አረንጓዴ ቀለም








## ቢጫ ቀለም





## ቀይ ቀለም






## ሰማያዊ ቀለም




### መልመጃ አስር

1. የሚከተሉት ምስሎች ምን ምን ቀለማት እንዳላቸው ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ።

1.



2.



3.



4.



5.



6.



7.



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ይህ ምዕራፍ ባህልን የተማርንበት ነው። ይህም ሲባል በአካባቢና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ጥበባትን ያየንበት ሲሆን በአካባቢያችን ውስጥ የሚገኙ ጥበባት ሲባል የሽክላ ስራ ውጤቶች ለምሳሌ ድስት፣ ምጣድ፣ እንስራና የመሳሰሉት ናቸው። ከሽመና ስራ ደግሞ ባህላዊ ቀሚሶች፣ ጋቢ፣ ኩታ፣ ሱሪና የመሳሰሉት ናቸው። ከስፌት ስራዎች መካከል ደግሞ ሞሰብ፣ ሰፌድ፣ ቁናና ሌሎችም የቤት ውስጥ መገልገያ ቅሳቁሶችን እናገኛለን።
- በአካባቢያችን ውስጥ ልዩልዩ ባህላዊ ዘፈኖች፣ ጭፈራዎችና ጨዋታዎች ይገኛሉ። ባህላዊ ዘፈኖች የምንላቸው በልዩ ልዩ በዓላት ላይ የሚዘፈኑ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል አበባየሁሽ አንዱ ነው። አበባየሁሽን የሚጫወቱት ሴት ልጆች ሲሆኑ የሆያ ሆየ ባህላዊ ጭፈራን ደግሞ ወንዶች በእንቁጣጣሽ በቡሄና በመሳሰሉት ህገራዊ በዓላት ላይ ይጫወታሉ።

- በአካባቢያችን ውስጥ ልዩ ልዩ ቀለማት ይገኛሉ። እነዚህ ቀለማት አካባቢያችን ልዩ ውበት እንዲኖረው ያደርጋሉ። ለምሳሌ በለበስናቸው ልብሶች ላይ የተለያዩ ቀለማት አሉ። እነዚህም ቀለማት ልብሶቻችን ከሌሎች ሰዎች ልብሶች ጋር ተመሳሳይ እንዳይሆን ስለሚያደርጉ የኔ ቀይ ነው። የጓደኛየ ቢጫ ነው። የመምህሬ አረንጓዴ ነው እንድንል ያስችለናል።
- በአካባቢያችን የሚገኙ አትክልቶች አረንጓዴ፣ አበቦች ቀይ፣ ቢጫ፣ እንዲሆኑ አድርጓል።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ከሚሰሩ ባህላዊ የመገልገያ ቁሳቁሶች መካከል በቤታችሁ የሚገኙትን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ባህላዊ ጨዋታዎች የሚባሉትን እንዴት መጫወት እንደሚቻል አስረዱ።
3. ከምታውቁት ተረት መካከል የምትወዱትን መርጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ።
4. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ቀለማት መካከል እናንተ የምትወዱት ቀለም የትኛው እንደሆነ ተናገሩ። የጠቀሳችሁትን ቀለም ለምን እንደወደዳችሁት አስረዱ።
5. ባህላዊ ዘፈኖችንና ጭፈራዎችን በቡድን በመሆን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

# ምዕራፍ 4

# ባህላዊ ተግባራትን ማድነቅ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በአካባቢያችሁ የሚዘወተር ባህላዊ አለባበስን ታደንቃላችሁ።
- ባህላዊ ቁሳቁሶችን በመጠቀም እቃ እቃ ቸዋታን ትጫወታላችሁ።
- ባህላዊ ጭፈራዎችን በተግባር ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- ባህላዊ ክንዋኔዎችን በስእል ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- ባህላዊ ክዋኔዎችን በስእል በመስራት ስሜታችሁን ትገልጻላችሁ።

## 4.1. ባህላዊ አለባበስ





## መዝሙር አስራ ስድስት፡-የኛ ጥበባት

የናቴ ነጠላ ጥበቡ
በቀለማት መዋቡ
በጣም አደነቅሁት
ማረከኝ ወደድኩት
የሰራውን ሰው አደንቀዋለሁ
እኔም እንደሱ መሆን እሻለሁ
ቤታችን ያሉ ሸክላ ስራዎች
የሀገራችን ጥበብ ውጤቶች
ያስደስቱኛል ይማርኩኛል
እኔም እነሱን መስራት ያሻኛል።

## 4.2 ባህላዊ ቁሳቁሶችን በመጠቀም መጫወት
















## 4.3 ባህላዊ ጭፈራን መጨፈር





**መልመጃ አስራ አንድ**

1. ባህላዊ አልባሳት መቼ መቼ ይለበሳሉ?
2. ባህላዊ አልባሳት ለምን ይጠቅማሉ?

## 4.4 ባህላዊ ተግባራትን መሳል













## የምዕራፉ ማጠቃለያ

✍ ይህ ምዕራፍ ባህላዊ ተግባራትን ያደነቅንበት ነው። ከነዚህም ባህላዊ ተግባራት መካከል ባህላዊ አለባበስ፣ ባህላዊ አጨፋፈር፣ አብሮ መብላት፣ መረዳዳትና ሌሎችም በአካባቢያችን የሚገኙ ባህላዊ ተግባራን በመተግበር አድንቀናል። እነዚህንም ባህላዊ ተግባራት በስእልና በመዝሙር እንደምንከባከባቸውና እንደምንጠብቃቸው ዘምረናል፣ በስእልም ስለናል።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ከሚሰሩ ባህላዊ የመገልገያ ቁሳቁሶች መካከል በቤታችሁ የሚገኙትን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ባህላዊ ተግባራት የሚባሉትን ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ።
3. ባህላዊ አልባሳት የሚባሉት ምን ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚሰሩ አስረዱ።
4. የምትወዱትን መዝሙር በቡድን በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ።
5. እናንተ የምትወዱትን ባህላዊ ተግባር ተናገሩ። ለምን እንደወደዳችሁት አስረዱ።

ምዕራፍ 5

# የሙዚቃ፣ የስዕልና የድራማ ግንኙነት(ዝምድና)

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የሙዚቃ፣ የስዕልና የድራማ ዝምድናን ታውቃላችሁ።
- የስዕል የሙዚቃንና የድራማን ዝምድና በስእልና በመዝሙር ትሰራላችሁ።
- የስዕል የሙዚቃንና የድራማን ዝምድና መዝሙር በመስማትና ስዕል በማየት ታደንቃላችሁ።

## 5.1 በቡድን መዘመር









## መዝሙር-አስራ ሰባት

## እኛም አለን ሙዚቃ

እኛም አለን ሙዚቃ -ስሜት የሚያነቃ(2)፣
መሰንቋችን -ዚኢ ዚኢ ዚኢ ዚኢ ዚኢ፣
ክራራችን -ክር ክር ክር ክር ክር፣
ከበሮችን -ቡም ቡም ቡም ቡም ቡም፣
ዋሽንታችን- ፊዉ ፊዉ ፊዉ ፊዉ ፊዉ።

### 5.1.1 ስለ ቀለማት መዝሙር







## መዝሙር አስራ ስምንት

## ቀለማት

ቀይ እንጆሪ አለኝ
ቢጫ ሙዝም አለኝ
እንጆሪ በልቸ ሙዜንም ጨምሬ
ከጓደኞቼ ጋር ልጫዎት አብሬ
ብርቱካናማዋን ብርቱካን እወዳለሁ
በአረንጓዴ ሳር ላይ እንከባለላለሁ
ሰማይ ላይ ሳንጋጥጥ ሰማያዊ አያለሁ
ሮዝ ቀለም ልፈልግ ጽጌሬዳን ልያት
ከጓደኞቼ ጋር በቀለም ልጫዎት።





## 5.1.2 ስለ ስዕል መዘመር

**መዝሙር አስራ ዘጠኝ**

**ስዕሌ**

ስእሌ ስዕሌ እኔ የፈጠርኩሽ
በእርሳሴ ሞንጭሬ እያሰማመርኩሽ
በቀለሞች ደግሞ ሳስዉብሽ
ሳስዉብሽ
እኔ እንደፈለኩኝ አሳምርሻለሁ
ቀለሞች ቀብቼ አስጌጥሻለሁ
የራሴ ስለሆንሽ
እኮራብሻለሁ።





## 5.2 በቡድን መተወን



## 5.3 መዝሙርን ትወናንና ስዕልን ማገናኘትና መተግበር





## የምዕራፉ ማጠቃለያ

✍በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እስከ ምዕራፍ አራት ያየናቸውን የእይታዊ ጥበብና የክዋኔ ጥበብ እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት በመዝሙርና በስእል የገለጽንበት ነው። ስእልና ሙዚቃ ተመሳሳይ ባህሪያት አሏቸው። ሁለቱም ጥበባት ፍቅርን፣ መውደድንና አድናቆትን ለመግለጽ ይረዱናል። ለምሳሌ በመዝሙር ስለ አካባቢ ባህል፣ ስለ ቤተሰብ ፍቅር፣ ስለ መከባበር በመዘመር መግለጽ ይቻላል። ስእልም በመሳል የቤተሰብን ፍቅር፣ የሀገርን ፍቅር፣ ባህሎቻችንን መግለጽ ያስችለናል።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ስለ ቀለም ከተዘመሩ መዝሙሮች መካከል የምትወዱትን መዝሙር በተናጠልና በጋራ በመዘመር ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ።
2. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርእስ መሰረት ድራማ በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አሳዩ።
3. የስእል፣ የሙዚቃንና የድራማን ግንኙነት ለመምህራችሁ ተናገሩ።
4. የስእል፣ የሙዚቃንና የድራማን ግንኙነት በመዝሙር አሰሙ።